# የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት

## መመሪያ 316/2013

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሰነድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE

የካቲት 2005
አዲስ አበባ

# የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ

## መግቢያ

የሀገራችን የገቢና የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓትን የተቀላጠፈና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ለማረጋገጥ ያስችላሉ ተብለው ከታመነባቸው ስትራቴጂዎች ውስጥ አንዱና ዋናው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ነው፡፡ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ በሀገራችን ከተጀመረ ረዥም ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም ወደ ጥናትና ተግባር የወረደው ግን በቅርብ ዓመታት ነው፡፡ ይህንንም ተከትሎ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የትግበራ ስምምነት በኢትዮጵያና በጅቡቲ መንግሥታት መካከል ተፈርሟል፡፡ በተጨማሪም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓትና የደረቅ ወደብ አገልግሎት ለመጀመር የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ በመቀናጀት በጋራ እና በተናጠል በርካታ እንቅስቃሴዎች ተከናውኗል፡፡

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በመተግበር የሚገኘው ሀገራዊ ፋይዳ ለማግኘትና ብሎም ለማሳደግ እንደዚሁም በአሠራር ላይ የሚታዩ ችግሮችን በወቅቱ ለመፍታት በመንግስት በኩል ልዩ ትኩረትና የቅርብ ክትትል በመደረግ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ትግበራ ላይ ያሉ ማነቆዎችን በመፍታት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚመራበት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊነት ታምኖበታል፡፡ የሥርዓቱ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ወሣኝ የሆኑና በሥርዓቱ እያጋጠሙ ያሉ ማነቆዎችና በቀጣይም ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ያስገባ የመፍትሄ አቅጣጫ ማስያዝ የግድ ይላል፡፡

ከዚህ አኳያ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በተፈለገው ደረጃ ዓላማውን ለማሳካት የሚያስችል መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ የሚመለከታቸው አካላት የተቀናጀ ሥራ መስራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚመራበትን ስታንዳርድ አሠራር ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው አካላት እስካሁን ተግባራዊ እያደረጉ የቆዩት ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ስርዓቱ ዓላማውን ያሳካ ዘንድ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነቶችና ግዴታዎች ለመወሰን እና የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999



ARCHIVE
Ministry of Transport

ለማስፈጸም፤ በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

# ክፍል አንድ - ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓትን ለማቀናጀትና ለመምራት የወጣ መመሪያ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

2.1. **የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት፡-** ማለት ቢያንስ በሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶች፣ ወጥ በሆነ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል መሰረት መልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሌላ አገር ውስጥ የሚገኝ የማስረከቢያ ቦታ ለማስረከብ የሚደረግ የማጓጓዝ ሥራ ነው፤

2.2. **መልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ፡-** ማለት ማንኛውም ሰው በራሱ ወይም በእሱ ስም በሚሰራ ሌላ ሰው አማካይነት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል የተዋዋለ እና ዋና ሆኖ የሚሰራ ወይም በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ክንውን የሚሳተፍ እና ስለ ውሉ አፈጻጸም ኃላፊ የሆነ ሰው ማለት ነው፤

2.3. **ደረቅ ወደብ ማለት ፡-** በሀገር ውስጥ ጭነቶች ሲገቡ የሚራገፉበት ቦታ እና አግባብነት ባለው ሕግ ተደንግጎ የተከለለ የጉምሩክ መ/ቤት ያለበት ቦታ ሲሆን በዚህ ክልል ውስጥ ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉትን ሕንጻዎች፣ ድርጅቶችና መሳሪያዎች ይጨምራል ፤

2.4. **የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ማለት፡-** ዕቃዎች ቀረጥ እስኪከፈልባቸው ድረስ የሚከማቹበትና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ፈቃድ የተሰጠው ማናቸውም ሥፍራ ሲሆን በተጨማሪ ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ሱቆችን ወይም

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪኮርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE

ቦንድድ የተደረገ የኤክስፖርት ፋብሪካዎችን ፤ ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዝን ፤ ቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዝንን ያጠቃልላል፡፡

2.5. **መዳረሻ ጣቢያ ማለት፡**-በሀገር ውስጥ ጭነቶች ሲገቡ የሚራገፉበት ደረቅ ወደብ፣የተፈቀዱ የጉምሩክና የቦንድድ መጋዘኖችን ይጨመራል

2.6. **የእፎይታ ጊዜ ፡-** ማለት በባህር ወደብ እና በደረቅ ወደብ ዕቃዎች ያለ መጋዘን ኪራይ እንዲቆዩ ለአስመጪዎች በወደብ ባለቤቶች በኩል የተፈቀደ ጊዜ ነው፡፡

2.7. **የመርከብ ውክልና** ማለት የመርከብ ባለንብረትን፤ ተከራይን፤ ወይም አከናዋኝ በመወከል፤ መርከቡ የሚያንጓዘውን ዕቃ ወይም መንገደኛ ማግኘትንና መመዝገብን፤ በባህር ወደብ ላይ እና በአገር ውስጥ ለመርከቦች አገልግሎት መስጠትን፤እንዲሁም መሰል ተግባራት ማከናወንን ይጨምራል፡፡

2.8. **የመርከብ ወኪል** ማለት በዕቃ አስተላላፊነት እና የመርከብ ውክልና ሥራ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁ.37/1990 መሠረት የመርከብ ውክልና ለመሥራት የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

2.9. **የመልቲሞዳል አከናዋኝ ፈቃድ፡-** መንግስት በሚሰጠው የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት መሰማራት ለሚፈልግ አካል በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

2.10. **ድርጅት** ማለት የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 255/2004 የተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፤

2.11. **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር** ፡- ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

2.12. **ባለሥልጣን፡-** ማለት በማሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 መሠረት የተቋቋመው የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፤

2.13. **ታሪፍ** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪነት የተሰማራ አከናዋኝ ከዕቃ ላኪ/አስመጪ ጋር ውል በገባበት ጊዜ የሚጠቀምበት የውል ሁኔታዎች ሆኖ ለሚሰጠው አገልግሎት የሚጠይቀውን የአገልግሎት ክፍያ የሚጨምር ነው፤

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሰነድና ማህደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

2.14. **የየብስ ወደብና ተርሚና ኦፕሬተር** ማለት የጉምሩክና ሌሎች ተቆጣጣሪ ተቋማትን ቢሮ ያሟላ፣ ለገቢና ለወጪ ዕቃዎች የመጫንና የማውረድ፣ እንዲሁም የመጋዘን አገልግሎት የሚሰጥበትን የየብስ ወደብ ተርሚናል በመገንባት የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡

2.15. **ሰው** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የመልቲሞዳል ትራንስፖርትን ሥርዓትን በተቀናጀ ሁኔታ ለመምራት እና የሎጅስቲክስ ሂደቱን የተሳለጠና ውጤታማ ለማድረግ ነው፡፡

## 4. አስፈጻሚ አካል

በአዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 7 ሥር በተደነገገው መሠረት የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት የሚመራበትን ስታንዳርድ አሠራር ለመወሰን የወጣውን ይህንን የአሰራር ሥርዓት የማስፈጸም ስልጣን እና ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚኖረው በማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት እንዲጓጓዙ በሚወሰኑ ዕቃዎች ላይ ነው፡፡

## 6. የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ኃላፊነትና ተግባር

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ባለስልጣኑ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

6.1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት የትራንዚት አገልግሎት አፈፃፀም ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ያሻሽላል፡፡

ARCHIVE

6.2. የመልሞዳል ትራንስፖርት ትግበራ ውጤታማ እንዲሆን በሥርዓቱ ሚና ያላቸው አካላትን ያቀናጃል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል።

6.3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የአገልግሎት አሰጣጥ ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር የሚያስችለውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የብቃት ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

6.4. ለመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በስታንዳርዱ መሰረት ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል።

6.5. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙን የአገልግሎት አሰጣጥና ታሪፍ ይቆጣጠራል።

6.6. በሀገር ውስጥ የደረቅ ወደቦች የሚገነቡበት ቦታ (location) ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው ያሳውቃል።

6.7. የማስተናገድ ዓቅምና ሌሎች ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የሚጓጓዙ ጭነቶችን ይወስናል፣

6.8. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ለመጠቀም የማይገደዱ (waiver) አስመጪዎች ዝርዝር ለመልቲሞዳል አከናዋኙ ይልካል፣

6.9. በሀገር ውስጥ የደረቅ ወደቦች የዕቃዎች ቆይታና አነሳስን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ያሻሽላል፣

6.10. የሀገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች የአገልግሎት የአፈፃፀም ስታንዳርድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ያሻሽላል።

6.11. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የትግበራ ሂደት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ይፈታል፣ ሥርዓቱ ይበልጥ ተመራጭ፣ ውጤታማና የተቀላጠፈ ለማድረግ የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ይነድፋል አሠራሮችን ተግባራዊ ያደረጋል፣

6.12. ከባህር ወደብ ባለስልጣናት ጋር በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የትግበራ ስምምነት ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱ ይከታተላል፣ በሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች ይፈታል ፤ የጅቡቲ ትራንዚት ማህበር የሞኖፖሊ አሠራር እንዲሻሻል የተሻለ አሠራር ተግባራዊ ያደርጋል፣

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት

6.13. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚጓጓዙ ጭነቶች መረጃ ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል ፤ ሀገራዊ የሎጅስቲክስ መረጃ ማዕከል ያደረጃል ፣ እንዲሁም አፈጻጸሙን ይገመግማል ለሚመለከታቸው አካላት የአፈጻጸም ሪፖርት ይልካል፡፡

## 7. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሰልጣን ሃላፊነትና ተግባር

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሰልጣን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

7.1. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ ጭነቶች ቀላል፣ አመቺና ወጥ የሆነ የትራንዚት ሠነድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ ያሻሽላል፣

7.2. በመልቲሞደል ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ ጭነቶች የቀረጥና የታክስ ዋስትና ይወስናል፣ ግልፅና የተቀላጠፈ አሠራር ይዘረጋል፣

7.3. በባህር ወደብ ከሚገኙ የጉምሩክ ባለስልጣናት ጋር በጋራ በመስራት የጉምሩክ የአሠራር ሥርዓቱ የተፋጠነ እንዲሆን ያደረጋል፣ በትግበራ ሂደት የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ይፈታል፣

7.4. በሀገር ውስጥ የደረቅ ወደቦች የጉምሩክ ፎርማሊቲ ለማጠናቀቅ የአሠራር ሥርዓቱ የተፋጠነ እንዲሆን ያደረጋል፣

7.5. የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶችና የተፈቀዱ የጉምሩክ መጋዘኖችን /Bonded Warehouse/ ዝርዝር በየጊዜው ለማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ይልካል

7.6. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የሚጓጓዙ ጭነቶች መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ይልካል፡፡

የ

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

## 8. የትራንስፖርት ባለስልጣን ሃላፊነትና ተግባር

ይህን መመሪያ በተመለከተ የትራንስፖርት ባለስልጣን የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡

8.1. እ.ኤ.አ በኖቬምበር 18 ቀን 2006 በጅቡቲና በኢትዮጵያ መንግስታት ጅቡቲ ላይ በተፈረመው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ትግበራ ስምምነት መሰረት የየብስ ትራንስፖርት አጓጓዦችን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል።

8.2. ከመልቲሞዳል ኦፕሬተሩ ጋር ውል የገቡ እና በውላቸው መሰረት ግዴታቸውን የማይወጡ አጓጓዦች ላይ በውሉ መሰረት የተዋዋለው አካል መብቱን በህግ ማስከበር እንደተጠበቀ ሆኖ የትራንስፖርት ባለስልጣን ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል።

## 9. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ኃላፊነትና ተግባር

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል።

9.1. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚጓጓዙ ጭነቶች ከባህር ወደብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያነሳል።

9.2. ከአስመጪው /ላኪው/ ጋር በገባው ውል መሰረት ጭነቶች የሚፈለጉበት ቦታ ያደርሳል።

9.3. በአከናዋኙ ሃላፊነት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ስለሚጓጓዙ ጭነቶች ዕለታዊ ዝርዝር መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ይልካል።

9.4. ጭነቶች መዳረሻ ጣቢያ ከመድረሳቸው በፊት ግምታዊ የዕቃ መድረሻ ጊዜ (Expected Time Arrival) ለአስመጪዎች ያሳውቃል

9.5. በአሰራር ሥርዓቱ ላይ በተቀመጡት የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት መረጃዎችን በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል።

9.6. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ለመጠቀም የማይገደዱ ወይም "waiver" የሚሰጣቸው ደንበኞችን በተመለከተ ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን



የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት ARCHIVE Ministry of ...

በሚተላለፈው መረጃ መሠረት ያስተናግዳል ፣ ለዚህም ግልጽ አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 10. የየብስ ወደብና ተርሚናል ኦፐሬተር ኃላፊነትና ተግባር

ይህንን መመሪያ በተመለከተ የየብስ ወደብ ተርሚናል ኦፐሬተር የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

10.1. በሀገር ውስጥ የየብስ ወደብ ተርሚናሎች በሚገነቡበት ቦታ ማስተር ፕላን መሠረት የየብስ ወደብ ተርሚናሎች ይገነባል፣ የማስተናገድ ዓቅም ያሳድጋል፣ ያሻሽላል፣

10.2. በሀገር ውስጥ በየብስ ወደብ ተርሚናሎች ውስጥ ዕቃዎችን ስለማስቀመጥና ማቆየት ለመወሰን የወጣው መመሪያን ተግባራዊ ያደረጋል፣

10.3. በአሰራር ሥርዓቱ ላይ በተቀመጡት የጊዜ ስታንዳርድ መሰረት መረጃዎችን በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

## 11. ብሔራዊ ባንክ

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ብሔራዊ ባንክ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

11.1. ከትራንስፖርት ሚንስቴርና ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን የሚወጡ መመሪያዎችን ለሁሉም ባንኮች በወቅቱ ያስተላልፋል፡፡

11.2. መመሪያዎቹ በሁሉም ባንኮች/የግልና የመንግስት/ ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል

11.3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓትን በተመለከተ በሁሉም ባንኮች ዘንድ ቀልጣፋ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣ ይከታተላል፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አስተዳደር
ARCHIVE
Ministry of Transport

## 12. ባንኮች

ይህንን መመሪያ በተመለከተ ባንኮች/የግልና የመንግስት/ የሚከተለው ሃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

12.1. በየዕለቱ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ለሚጓጓዙ ጭነቶች የተሰጡ የባንክ ፈቃዶች መረጃ ለማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ያስተላልፋሉ

12.2. የባንክ ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት የአስመጪዎችን/የላኪዎችን የተሟላ አድራሻ ይመዘግባሉ፤

12.3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓትን ቀልጣፋ ለማድረግ ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡

## 13. የማስፈጸሚያ ስልት

ከዚህ መመሪያ ጋር በክፍል ሶስት አባሪ ሆኖ የተያያዘው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ስታንዳርድ የመመሪያው አካል ሆኖ ይፈጸማል፡፡

## 14. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ--------ቀን 2005 ዓ.ም

ድሪባ ኩማ

የትራንስፖርት ሚኒስትር

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport

# ክፍል ሶስት

## የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት አፈጻጸም ስታንዳርድ

### መግለጫ

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ስታንዳርድ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት መመሪያ ለማስፈጸም እና በመመሪያው ውስጥ ሃላፊነትና ተግባር የተሰጣቸው አካላት ኃላፊነቶቻቸውን በአግባቡ ማከናወናቸዉን ለመከታተልና አፈጻጸማቸውን ለመለካት እንዲያስችል ይህ ወጥ የሆነ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡

ስታንዳርዱ ሲዘጋጅ በዋናነት መሰረት ያደረገዉ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የትራንዚት ጊዜ እና ወጪን ከመቀነስ አንጻር የተደረጉ ግምገማዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ስታንዳርዱ የስራው ሂደት የሚወስደውን ጊዜ እንዲሁም የተግባሩን ፈጻሚ አካል በግልጽ በማስቀመጥ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ሪከርድና ማኅደር አገልግሎት
ARCHIVE
Ministry of Transport